# ዋሽንግተን

**በዋሽንግተን ላይ የተመሰረተ የማኅበር አባላት የቢሆን ትንታኔ እና የሚገኙ ጥቅማጥቅሞች**

| **1199NW የአባል የቢሆን ትንታኔ** | **PFMLA** | **የሰራተኞች ክፍያ (L&I)** | **ሥራ አጥነት** | **ፌዴራል ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የመቅረት ፈቃድ (FFCRA)** |
|---|---|---|---|---|
| **ዝቅተኛ የሕዝብ ቆጠራ** | | | X | |
| **ክፍሉ ተዘግቷል፣ ሌላ ሥራ የለም** | | | X | |
| **ክፍሉ ተዘግቷል፣ ሌላ የሥራ ግብዣን አልተቀበሉም** | | | (ለምን እንዳልተቀበሉ ባቀረቡት ምክንያት ላይ ይወሰናል) | |
| **ዕለታዊ ክፍያ፣ የተለመዱ ሰዓቶችን እየተቀበሉ አይደለም** | | | X | |
| **የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም ተዳክሟል** | ምናልባት። መሥራት ከቻሉ UI ይጠቀሙ | | X | |
| **ክፍሉ በሽታ የመከላከል አቅሙ ተዳክሟል** | ምናልባት | | | |
| **ተለይቶ ተቀምጧል** | | X | X | X |
| **የኮቪድ-19 በሽተኛ** | X | X | | X |
| **ለልጆች እንክብካቤ ሲባል የቀሩ** | | | መሥራት በመቻልዎ (ለምሳሌ ከሩቅ) ላይ ይወሰናል | X |

አጠቃላይ

1. የስቴት ወይም ፌዴራል ጥቅማጥም እየተቀበልሁ ከሆነ፣ ወይም ለመቀበል ተስፋ ያለኝ ከሆነ፣ ከሥራ ውጭ የቆየሁበት የተጠራቀመ ጊዜ ለማሟያነት በዚህ መጠን ላይ ሊታከል ይችላል?

- PFMLA፣ ፌዴራል የሚከፈልበት FMLA፣ ፌዴራል የሚከፈልበት የህመም ፈቃድ፣ የሰራተኞች ክፍያ L&I፡- ክፍያዎችዎን ሙሉ ለማድረግ ያለውን ጉድለት ለመሙላት፣ የተጠራቀሙ ጥቅማጥቅሞችን ወይም የአሰሪ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ አስተዳደራዊ ፈቃድን መቀበል ይችላል እንደ ማኅበር፣ ሰዎች የክፍያ ጉድለታቸው እንዲሟላ ሰራተኞች ከክፍያ ጋር የሚሰጥ አስተዳደራዊ ፈቃድ እንዲያቀርቡ እንዲሁም እንደ አማራጭ፣ የተጠራቀመ ፈቃዳቸውን እንዲያገኙ ግፊት እናደርጋለን፣ ነገር ግን የተወሰኑት ገና አልተስማሙም።
- ከሥራ ውጭ መሆን ከሥራ የተቀነሱ ከሆኑ፣ ወይም የሥራ ሰዓትዎ የተቀነሰብዎ ከሆነ እና የሥራ እጦት ጥቅማጥቅሞች እየተቀበሉ ከሆነ፣ ከሥራ ውጭ ሆነው በቆዩባቸው ጊዜያት ከአሰሪዎ የተቀበሏቸው ማናቸውም ክፍያዎች ሪፖርት መደረግ አለባቸው፣ ከዚያም የሥራ እጦት ጥቅማጥቅሞችዎ ከክፍያ ጋር በሚሰጥ ፍቃድ መልክ በተቀበሉት መጠን ልክ ይቀንሳል፣ ስለዚህ ይህ ጉድለትዎን ለማሟላት ጥሩ፡ አማራጭ አይደለም።

2. FFCRAን ማን መጠቀም ይችላል?

- ቅድሚያ ለቤተሰብ የኮሮናቫይረስ ምላሽ ድንጋጌ (FFCRA) ይህ ሕግ የሚሰራው ለመንግስት አሰሪዎች እና ከ 500 ሰራተኞች በታች ላላቸው የግል አሰሪዎች ነው። FFCRA ሽፋን ላላቸው ሰራተኞች የጤና ክብካቤ አቅራቢዎችን (ሁሉንም የሆስፒታል እና የአረጋውያን ክብካቤ ማዕከላት ሰራተኞችን ጨምሮ) ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ነጻ ያደርጋል፣ ነገር ግን የጤና ክብካቤ አቅራቢዎች አሰሪዎች አሁንም ቢሆን በFFCRA ውስጥ የተቀመጡ ትቅማጥቆምችን ለማቅረብ ከመረጡ፣ ያንን ማድረግ ይችላሉ።
    - ጥቅማጥቅሞች፡- (1) መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰራተኞች፣ ከቪድ-19 በምርመራ ከተገኘባቸው፣ ወይም ምልክቱን ካሳዩ እና ምርመራ እየተጠባበቁ ከሆነ እስከ 80 ሰዓት የሚደርስ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ በሙሉ የክፍያ ተመናቸው ሊያገኙ ይችላሉ፤ (2) መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰራተኞች ተለይቶ በመቆየት ላይ ላለ ሰው ክብካቤ ለማቅረብ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ ወይም የቀን መቆያው ከኮቪድ-19 ጋር ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች በመዘጋቱ ክብካቤ ለማቅረብ በመሳሰሉ ሐቀኛ ምክንያቶች መስራት ካልቻሉ፣ ከሚከፈላቸው መደበኛ ክፍያ ሁለት ሶስተኛ በሆነ ተመን እስከ 80 ሰዓታት ከክፍያ ጋር የሚሰጥ እረፍት ሊያገኙ ይችላሉ፤ እንዲሁም (3) መስፈርቱን የሚያሟሉና ቢያንስ ለ30 ቀናት በሥራ ላይ የቆዩ ሰራተኞች፣ ከኮቪድ-19 ጋር ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች ትምህርት ቤቱ ወይም የዕለት መቆያው ለተዘጋበት ሕጻን ክብካቤ እንዲያቀርቡ እስከ 10 ተጨማሪ ሳምንታት የሚደርሱ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የቤተሰብ እና የሕክምና ፈቃድ ከመደበኛው የክፍያ ተመናቸው ሁለት-ሶስተኛ ሊያገኙ ይችላሉ።

3. የቀረበልኝን ሥራ ካልተቀበልኩ፣ ክፍያ ለመቀበል ያሉኝ አማራጮች ምንድናቸው?

- የሚከተሉት እርምጃዎች የቀረበልዎትን ሥራ ለምን እንዳልተቀበሉ በሚሰጡት ምክንያት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡-
    - እራስዎ ወይም የሚወዱት ሰው በመታመሙ ምክንያት አሁኑኑ መሥራት ባለመቻልዎ ምክንያት ከሆነ፣ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ አስተዳደራዊ ፈቃድ የሌለ ከሆነ፣ PFMLA የተሻለው አማራጭዎ ሊሆን ይችላል።
    - ውስጣዊ የጤና እክል ስላለብዎና እንዲሰሩ የተጠየቁትን ሥራ ለመስራት ደህንነት የማይሰማዎ እና መስራት የማይችሉ በመሆኑ ምክንያት ከሆነ፣ እንዲሁም አሰሪዎ ሸርችዋል ወይም ከሩቅ

የሚሰሩበትን አማራጭ ካላቀረበልዎ፣ ከሥራ ውጭ መሆን አማራጭ ሊሆን ይችላል። ከሕክምና አቅራቢዎ በውስጣዊ የጤና እክል ምክንያት በቤት ውስጥ መቆየት እንዳለብዎ የሚገልጽ ማስታወሻ እንዲቀበሉ በጽሁ ይመከራሉ።

4. ከልጄ (ልጆቼ) ጋር በቤት ውስጥ መቆየት አለብኝ። ምን የመረጃ ምንጮች ይገኛሉ?

- የሚሰሩት ለመንግስት ቀጣሪ ወይም ከ 500 ሰራተኞች በታች ላሉት የግል ቀጣሪ ከሆነና እንደ ጤና ክብካቤ አቅራቢ እርስዎን ከPFMLA ጥቅማጥቅም ውጭ ላለማድረግ ከተስማሙ፣ የልጅዎ (የልጆችዎ) ትምህርት ቤት ወይም የሕጻናት ማቆያ ከኮቪድ-19 ጋር ተያያዥ በሆነ ምክንያት ከተዘጉ፣ ከክፍያ ጋር ለሚሰጥ የሕክምና ፈቃድ እና የዚያ ሕግ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የቤተሰብ እና ሕክምና ፈቃድ ደንቦች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከሲያትል ውጭ ከሆኑ፣ ለሕጻናት ክብካቤ ምንጮች በስልክ ቁጥር 1-800-446-1114 ይደውሉ።
- [የDSHS ጣቢያ ለ *ስለ ሕጻናት ክብካቤ ግንዛቤ ያላቸው ቤተሰቦች፣ ጓደኞች እና ጎረቤቶች ፕሮግራም*አገናኝ እና ለጤና ክብካቤ ሰራተኞች ዲስቲክት-በ-ዲስትሪክት የሕጻናት ክብካቤ የሚገኝበቸውን የዋሽንግተን ካርታ ይዟል።]
- ዋና የክብካቤ አቅራቢ ከሆኑና ልጅ (ወይም እርስዎ ዋናው እንክብካቤ አቅራቢ የሆኑለት ሌላ የቤተሰብ አባል) በኮቪድ-19 ቀጥተኛ ምክንያትነት በትምህርት ቤት ወይም በሌላ ተቋም መገኘት ካልቻለ፣ በCARES ሕግ እና የወረርሽኝ ሥራ እጦት ድጋፍ (PUA) መሰረት ለሥራ እጦት መድን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

5. ለጊዜው ቀጥተኛ የሕመምተኛ ክብካቤ ሥራ ለመስራት ስጋት ገብቶኛል፣ ምክንያቱም እኔ ወይም የቅርብ ሰው የበሽታ መከላከል አቅም ተዳክሟል፣ አሰሪዬ ደግሞ የቨርችዋል ሥራ አማራጭ አልሰጠኝም። የስቴት/ፌዴራል ጥቅማጥቅሞችን መጠየቅ አለብኝ?

- ከክፍያ ጋር የሚሰጥ አስተዳደራዊ ፈቃድ ከሌለ፣ ለሥራ እጦት ማመልከት ይችላሉ - ከሕክምና አቅራቢዎ በቤት ውስጥ መቆየት እንዳለብዎ የሚመክር ማስታወሻ እንዲቀበሉ በጽኑ የመከራል።
- መስራት የማይችሉ ከሆነ፣ እርስዎ ወይም በእርስዎ ላይ የሚደገፈው ሰው በሽታን የመከላከል አቅም በመዳከሙና ነገር ግን በሥራ ላይ በመቆየቱ ምክንያት ሕመም ላይ ቢወድቅ፣ ለPFMLA ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

6. በሥራ እጦት፣ የሰራተኛ ካሳ፣ PFMLA፣ ወይም ሌላ ዘዴ አማካኝነት ለማንኛውም ድጋፍ ብቁ ነኝ ብዬ አላስብም። ሌሎች አማራጮች አሉ?

- ገዥ ኢንስሊ የስደተኛ እርዳታ ፈንድ መፈጠሩን አሳውቀዋል፣ ይኸም በስደተኝነት ሁኔታቸው ምክንያት ሌሎች የፌዴራል እና ስቴት ፕሮግራሞች ሊደርሳቸው ለማይችሉ የዋሽንግተን ነዋሪዎች $40 ሚሊዮን የሚያቀርብ ነው። በአሁኑ ጊዜ የዋሽንግተን ስቴት ዲፓርትመንት ማኅበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች፣ አትራፊ ላልሆኑ ድርጅቶች ፈንዱን እንዲያስተዳድሩ የምክረ-ሐሳብ ጥያቄ አቅርቧል፣ ከዚያም የተመረጠው ድርጅት ከማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለገሳውን ለግለሰቦች ያድላል። ብቁ የሆኑ ግለሰቦች $1000 ያገኛሉ። ይህ ገንዘብ በመጪው ጸደይ ሊደርስ ይችላል። [ስለ ስደተኛ እርዳታ ፈንድ ተጨማሪ መረጃ እዚህ ይገኛል።]
- በኦገስት ውስጥ፣ DSHS ሰዎች ፣ በአደጋ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም አማካኝነት የዜግነት ሁኔታቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ ሊያመለክቱ የሚችሉበት የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም ያካሂዳል፣ ይኸም በሌሎች

የእርዳታ ወይም የገቢ ድጋፍ ላይ ለመሳተፍ ብቁ ላልሆኑ ሰዎች የታሰበ ነው። የዚህ ገንዘብ መጠን እንደ ቤተሰብ መጠን እና ፍላጎት ከ $363 እስከ $1,121 የሚደርስ ሲሆን፣ በ12 ወራት አንድ ጊዜ ይገኛል። [የማመልከቱን ሂደት ለመጀመር WashingtonConnection.org ን ይጎብኙ።](WashingtonConnection.org).

- 7. ሌሎች ምን ድጋፎች አሉ?
- የዋሽንግተን ንግድ ዲፓርትመንት የኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም ለማከናወን $100 ሚሊዮን እያሰራጨ ነው፤ ይኸም እስከ 3 ወራት ድረስ ውዝፍ ኪራይ፣ የአሁን ተከፋይ ኪራይ እና የወደፊት ኪራይን ለአከራዮች በመክፈል ከቤት ማስወጣትን በመከላከል ላይ ያተኮረ ነው። ፕሮግራሙ የተጀመረው ኦገስት 1 ሲሆን የሚያበቃው በዲሴምበር 31, 2020 ነው። መረጃ፣ የፕሮግራም መምሪያዎችን እና ቅጾችን ጨምሮ፡- ዋሽንግተን ስቴት የንግድ ዲፓርትመንት – ከቤት ማስወጣትን ለመከላከል የኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም።
- ተጨማሪ ድጋፎች በዚህ ዝርዝር ውስጥ ተዘርዝረዋል በኮቪድ-19 ለተጠቁ የዋሽንግተን ነዋሪዎች የDFI የገንዘብ ምንጮች።

የሥራ እጦት

የሥራ ደህንነት ዲፓርትመንት (ESD) በማርች 8 እና ጁን 18 መካከል የገቡ ማመልከቻዎችን እስከ ጁላይ 31 ለመጨረስ ሰርቷል፣ በመሆኑም ለሁሉም ማመልከቻዎች መፍትሔ ሰጥቷል። ለሥራ እጦት አመልክተው ከሆነ፣ እና እስካሁን ካላገኙ፣ እባክዎ COVIDLegalAid@seiu1199nw.orgን ያግኙ -- እባክዎ ስላሉበት ሁኔታዎ አጭር መግለጫ፣ የመጀመሪያ ማመልከቻዎን ያስገቡበትን ቀን እና የጠያቂ መለያዎን ያካትቱ።

ተጨማሪ $600 በየሳምንቱ እንዲሰጥ የሚፈቅደው PCARES ሕግ ጁላይ 25 ላይ ጊዜው አብቅቷል። የወደፊት የእርዳታ ጥቅሎች ተጨማሪ ገንዘብ ለሥራ እጦት ብቁ ለሆኑ ሰዎች ሊፈቅዱ ይችላሉ፡ በዚህ ገጽ ላይ የሚኖሩ ለውጦችን እየተከታተልን ለማዘመን እንሰራለን።

8. የሥራ እጦቴ የሚጀምረው መቼ ነው?

- ዋሽንግተን የአንድ-ሳምንት የመጠበቂያ ጊዜን አንስቷል፣ ስለዚህ ጥቅማጥቅሞች ማመልከቻዎን ካስገቡበት ቀን ጀምሮ መጀመር አለባቸው።

9. የሥራ እጦት መቀበል የምችለው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

- መደበኛው የዋሽንግተን የሥራ እጦት ጥቅማጥቅም ቆይታ 26 ሳምንታት ነው፣ ነገር ግን በፌዴራል የሥራ እጦት አማራጮች መሰረት፣ ጥቅማጥቅሞች በአጠቃላይ እስከ 46 ሳምንታት ድረስ ሊቀበሉ ይችላሉ - በግምት ለ10 ከ ግማሽ ዓመታት ማለት ነው።

10. PFMLA እና የሥራ እጦት  መድን በተመሳሳይ ጊዜ መቀበል እችላለሁ?

- አይችሉም፣ PFMLA የሚያገለግለው በከባድ የጤና ሁኔታ ምክንያት ወደ ሥራ መመለስ ለማይችሉ ሰዎች ነው። የሥራ እጦት የሚያመለክተው ሥራ መስራት መቻልዎን እና ወደ ሥራ መመለስ እንደሚችሉ ወይም አዲስ ሥራ እየፈለጉ እንደሆነ ነው።

11. በመደበኛ የሥራ እጦት እና በተጋራ ሥራ ስምምነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

- አሰሪዎች፣ ከሥራ መቀነስን ለመቀነስ፣ የሰራተኛ ቁጥርን መቀነስ ከፈለጉ ለESD የተጋራ ሥራ ፕሮግራም ማመልከት ይችላሉ። የሥራ ሰዓቶቻቸው የተቀነሱባቸው፣ ነገር ግን ከመደበኛው ስራቸው ከ50%-90% እየሰሩ የሚገኙ ሰራተኞች አሰሪያቸው ለዚያ አመልክቶ ከሆነ በተጋራ ሥራ ፕሮግራም አማካኝነት ተመጣጣኝ የሥራ እጦት ጥቅማጥቅሞችን ሊያገኙ ይችላሉ።
- አሰሪው ክንውኖችን እየቀነሰ ከሆነና ስለዚህም የሰራተኞችን ሰዓቶች እየቀነሰ ከሆነ፣ ሰራተኞቹ በሳምንት ቢያንስ 16 ሰዓት እስከሰሩ ድረስ፣ አሰሪው "ከፊል" የሥራ እጦት ለሰራተኞቹ መጠየቅ ይችላል።

## ሞንታና

Montana-based 1199NW የአባል የቢሆን ትንታኔዎች እና የሚገኙ ጥቅማጥቅሞች

| 1199NW የአባል የቢሆን ትንታኔ | የሰራተኞች ካሳ | ሥራ አጥነት | ፌዴራል ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የሕክምና ፈቃድ እና FMLA |
|---|---|---|---|
| ዝቅተኛ የሕዝብ ቆጠራ | | X | |
| ክፍሉ ተዘግቷል፣ ሌላ ሥራ የለም | | X | |
| ክፍሉ ተዘግቷል፣ ሌላ የሥራ ግብዣን አልተቀበሉም | | ለምን እንዳልተቀበሉ ባቀረቡት ምክንያት ላይ ይወሰናል | |
| ዕለታዊ ክፍያ፣ የተለመዱ ሰዓቶችን እየተቀበሉ አይደለም | | ምናልባት | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የሰውነት በሽታ የመከላከል አቅም ተዳክሟል** | | ወደ ለይቶ ማቆያ ከተመሩ ብቻ | |
| **ክፍሉ በሽታ የመከላከል አቅሙ ተዳክሟል** | | ጥገኛው ታማሚ ወይም ወደ ለይቶ ማቆያ የተመራ ከሆነ | |
| **ተለይቶ ተቀምጧል** | | X | አዎ፣ በ FFCRA የፌዴራል ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የሕክምና ፈቃድ በኩል፣ ሁሉም ያልተከፈለ FMLAም ዘንድ መድረስ መቻል አለብዎ |
| **የኮቪድ-19 በሽተኛ** | በሥራ ላይ የተያዙ ከሆነ | | አዎ፣ በ FFCRA የፌዴራል ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የሕክምና ፈቃድ በኩል፣ ሁሉም ያልተከፈለ FMLAም ዘንድ መድረስ መቻል አለብዎ |
| **ለልጆች እንክብካቤ ሲባል የቀሩ** | | X | በFFCRA በኩል ብቻ የፌዴራል ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የሕክምና ፈቃድ |

- ሞንታና ውስጥ፣ የሥራ እና ኢንዱስትሪ ዲፓርትመንት (L&I) የሰራተኞች ካሳ እና የሥራ እጦት መድንን ሁለቱንም ይመለከታል
- የፌዴራል ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የሕክምና ፈቃድ የሚከናወነው በቅድሚያ ለቤተሰብ የኮሮናቫይረስ ምላሽ ሰጪ ሕግ (FFCRA) አማካኝነት ነው። FFCRA እንደ አሰሪ KRHን አይሸፍንም ስለሆነም አባላት ያንን ማግኘት አይችሉም። ተጨማሪ  መረጃ ፦ FFCRA ከታች ከ13 ቁጥር ቀጥሎ ነው።
- የሰራተኞች ካሳ አብዛኞቹን በኮቪድ-19 ሊያዙ የሚችሉ ሰራተኞችን አይሸፍንም፤ ነገር ግን ለ "ሽፋን ባለው ቅጥራቸው አማካኝነት ከፍተኛ የተጋላጭነት አደጋ ባለበት ቦታ ላይ የተመደቡ ጤና ክብካቤ እና የድንገተኛ ሕክምና አገልጎቶች (EMS) ሰራተኞች" በልዩ ሁኔታ ይታያል።
- በCARES ሕግ መሰረት ተጨማሪ $600 ሳምንታዊ ክፍያ የሚፈቅደው ደንብ በጁላይ 25 ጊዜው አብቅቷል። የወደፊት የእርዳታ ጥቅሎች ተጨማሪ ገንዘብ ለሥራ እጦት ብቁ ለሆኑ ሰዎች ሊፈቅዱ ይችላሉ፡ በዚህ ገጽ ላይ የሚኖሩ ለውጦችን እየተከታተልን ለማዘመን እንሰራለን።

12. ለሥራ እጦት ማመልከት ጀምሬ ነበር እናም የማኅበር አባል ስለመሆኔ ሶስት ጥያቄዎች አጋጠሙኝ። ይኽን እንዴት ነው የምሞላው?

- ለመጀመሪያው ጥያቄ፣ "የማኅበር አባል ነዎት"፣ አዎ ወይም አይን መምረጥ ይችላሉ። የKRH/KRMC RNs አባላትን በማኅበራችን ውስጥ እንዳሉ እንቆጥራለን፣ እንዲሁም አሁን የመጀመሪያውን ኮንትራትዎን

በመደራደር ሂደት ላይ ነዎት፣ ስለሆነም የማኅበር ወዋጮ እየከፈሉ አይደለም። ለሁለተኛው እና ለሶስተኛው ጥያቄ፣ ሁለቱም “አይ” ተብለው መመለስ አለባቸው።

13. በኮቪድ-19 ለተጎዱ ሰዎች እያደገ የሚሄድ ጥቅማጥቅምን የሚመለከቱ አዲስ የፌዴራል ሕጎች የትኞቹ ናቸው?

- ቅድሚያ ለቤተሰብ የኮሮናቫይረስ ምላሽ ድንጋጌ (FFCRA) ይህ ሕግ የሚሰራው ለመንግስት አሰሪዎች እና ከ 500 ሰራተኞች በታች ላላቸው የግል አሰሪዎች ነው። FFCRA ሽፋን ላላቸው ሰራተኞች የጤና ክብካቤ አቅራቢዎችን፣ ሁሉንም የሆስፒታሎች እና የአረጋውያን ክብካቤ ማዕከል ሰራተኞች ጨምሮ) ከደንቦቹ ነጻ የመሆን አማራጭ አቅርቧል፣ ነገር ግን የጤና ክብካቤ አቅራቢዎች፣ ፍላጎቱ ካላቸው፣ በFFCRA ውስጥ የተጠቀሱ ጥቅማጥቅሞችን ለጤና ክብካቤ ሰራተኞቻቸው ማቅረብ ይችላሉ።
    - ጥቅማጥቅሞች፡- (1) መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰራተኞች፣ ኮቪድ-19 በምርመራ ከተገኘባቸው፣ ወይም ምልክቱን ካሳዩ እና ምርመራ እየተጠባበቁ ከሆነ እስከ 80 ሰዓት የሚደርስ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ በሙሉ የክፍያ ተመናቸው ሊያገኙ ይችላሉ፤ (2) መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰራተኞች ተለይቶ በመቆየት ላይ ላለ ሰው ክብካቤ ለማቅረብ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ ወይም የቀን መቆያው ከኮቪድ-19 ጋር ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች በመዘጋቱ ክብካቤ ለማቅረብ በመሳሰሉ ሐቀኛ ምክንያቶች መስራት ካልቻሉ፣ ከሚከፈላቸው መደበኛ ክፍያ ሁለት ሶስተኛ በሆነ ተመን እስከ 80 ሰዓታት ከክፍያ ጋር የሚሰጥ እረፍት ሊያገኙ ይችላሉ፤ እንዲሁም (3) መስፈርቱን የሚያሟሉና ቢያንስ ለ30 ቀናት በሥራ ላይ የቆዩ ሰራተኞች፣ ከኮቪድ-19 ጋር ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች ትምህርት ቤቱ ወይም የዕለት መቆያው ለተዘጋበት ሕጻን ክብካቤ እንዲያቀርቡ እስከ 10 ተጨማሪ ሳምንታት የሚደርሱ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የቤተሰብ እና የሕክምና ፈቃድ ከመደበኛው የክፍያ ተመናቸው ሁለት-ሶስተኛ ሊያገኙ ይችላሉ።

14. ለFMLA ብቁ እሆናለሁ፣ ከሆንኩስ፣ የ ለእኔ ምን ማለት ነው?

- FMLA ተፈጻሚ የሚሆነው ለሕዝብ ኤጀንሲዎች እና ለአብዛኞቹ የግል ዘርፍ ሰራተኞች ነው። ብቁ ለመሆን፣ አንድ ሰራተኛ ከፍቃድ ሙከራው በፊት በ12 ወራት ውስጥ 1,250 ሰዓታት የሰራ እና ለአሰሪው ቢያንስ ለ12 ወራት የሰራ መሆና አለበት። FMLA ሰራተኞች እስከ 12 የሥራ ሳምንታት የሚደርስ ያለክፍያ፣ ጥበቃ የሚደረግለት ፈቃድ እንዲያገኙ ይፍቀዳል፣ ይኽንንም አሰሪው የካላንደር ዓመት አድርጎ፣ ወይም በዓመቱ ውስጥ በአንዱ የተወሰነ ቀን በየዓመቱ የሚታደስ ቀን አድርጎ ሊወስደው ይችላል። የ12 የፈቃድ ሳምንታት ሁሉም በአንድ ጊዜ ሊወሰዱ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ተከፋፍለው ሊወሰዱ ይችላሉ።
- ሰራተኞች FMLAን ለሚከተሉት ምክንያቶች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡-
    - ወሊድ እና/ወይም ድህረ ወሊድ የጨቅላ ክብካቤ ጊዜ፤
    - ልጅን ለጉዲፈቻ ወይም ለአደራ ማደጎ መስጠት እና ከዚያ ሕጻን ጋር የመወዳጃ ጊዜ፤
    - ከባድ የጤና እክል ላለበት የቅርብ የቤተሰብ አባል ክብካቤ ለማድረግ (የትዳር ጓደኛ፣ ልጅ፣ ወይም ወላጅ (አማቾችን አይጨምርም))፤
    - በከባድ የጤና እክል ምክንያት ሰራተኛው ሥራ መስራት የማይችል በሚሆን ጊዜ የሕክምና ፈቃድ ለመውሰድ

- “የሰራተኛው የትዳር ጓደኛ፣ ልጅ፣ ወይም ወላጅ እንደ ብሔራዊ ዘብ፣ ሪዘርቮች ወይም መደበኛ የጦር ኃይሎች አባል ሽፋን ባለው የስራ ግዳጅ ወይም ሽፋን ላለው የሥራ ግዳጅ በተጠባባቂ ሁኔታ ላይ ያለ መስፈርቱን የሚያሟሉ ድንገተኛና አስቸኳይ ክስተቶች።
- ያስታውሱ፣ FMLA ከክፍያ ውጪ የሚወሰድ ፈቃድ ነው ሰራተኞች ከተጠራቀሙ ባንኮች፣ ወይም በኮቪድ-19 በመያዛቸው ወይም የእነርሱ ጥገኛ በመያዙ ምክንያት FMLA የሚጠይቁ አባላትን ለመደገፍ ከአሰሪዎቻቸው ጋር የተደረጉ ስምምነቶች ካሉ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ አለ።

15. ስለ ጥቅማጥቅም እና የገንዘብ ድጋፍ ተጨማሪ ምንጮችን ከየት እናገኛለን?

ሞንታና L&I ዲፓርትመንት፡- COVID-19 Resources for Montana Employees

ሞንታና ስቴት ዲፓርትመንት Governor’s Coronavirus Task Force

ሞንታና L&I ዲፓርትመንት፡- Scenarios & Benefits Available